በስመ አብ ወወልደ ወመንፈስ ቅዱስ

አሐዱ አምላክ

አሜን

ትምህርተ ድንግል ማርያም



አስተጋብአተነ እግዝእትነ ወላዲተ አምላክ

መጋቢት ፭1//////////// ፭፻፲3 ዓ.ም

የነገረ ማርያም ትምህርት ዋና ዓላማ

❖ **ሥላሴ የተገለጡባት ስለሆነች ምሥጢረ ሥላሴን በሚገባ ለመረዳት**

- እንዲሁም እመቤታችን ምሥጢረ ሥላሴ የተገለጠባት ናት። መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፣ የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል፣ ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል”
- እግዚአብሔር አብ፣ እግዚአብሔር ወልድ፣ ፣ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ሦስቱም በእመቤታችን ላይ ተገልጠዋል።
- “በአንቺ ላይ ይመጣል” የተባለው መንፈስ ቅዱስ፣ “የልዑል ኃይል ይጸልልሻል” የተባለው እግዚአብሔር አብ፣ “ከአንቺ የሚወለደው ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ” የተባለው እግዚአብሔር ወልድ በእርሷ ላይ ተገልጠዋል።
- ይህ የሆነውም በዮርዳኖስና በደብረ ታቦር ከተፈጸመው የቅድስት ሥላሴ የመገለጥ ምሥጢር አስቀድሞ ነው።
- ነቢዩ ዳዊት **“ወያስተርኢ አምላክ አማልክት በጽዮን - የአማልክት አምላክ በጽዮን ይታያል”** ብሎ የተናረው ትንቢት ተፈጸመ። **መዝ. 83፡7**

እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ምን ያህል እንደ ወደደው በተጨባጭ ሁኔታ ፍቅረ እግዚአብሔርን የምታሳየን ስለሆነች

- “እግዚአብሔር ሰውን ምን ያህል ይወደዋል?” ብለን ብንጠይቅ ድንግልን እናቱ እስከ ማድረግና ከእርሷ እስከ መወለድ ድረስ የሚል መልስን ከድንግል ማርያም እናገኛለን።
- እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም - እግዚአብሔር የሰውን ባሕርይ ምን ያህል እንዳከበረው፣ የራሱ አካል የራሱ ባሕርይ እስኪያደርገው ድረስ ያከበረው መሆኑን በተግባር የምትመሰክር ሕያዊት ምስክር ናት።
- ተዓምሯን ስናስብ፣ ምስለ ፍቁር ወልዳ ሥዕሏን ስናይ፣ - እግዚአብሔር ቃል የእኛን ባሕርይ ባሕርዩ አካላችንን አካሉ ማድረጉን፣ ለእኛ የተሰጠው ክብር ከመነገር ከመታሰብ በላይ ልዩና ድንቅ መሆኑን እንረዳበታለን፣ በተዘክሮ እንመሰጥበታለን

❖ልዩ የሕይወትና የተግባር አርአያና መምህራችን ናት።

- እናንተ ጽድቅን የምትከተሉ እግዚአብሔርንም የምትሹ፥ ስሙኝ፤ ከእርሱ የተቈረጣችሁበትን ግንድ ከእርሱም የተቈፈራችሁበትን ጕድጓድ ተመልከቱ። ወደ አባታችሁ ወደ አብርሃም፥ ወደ ወለደቻችሁም ወደ ሳራ ተመልከቱ” **ኢሳ. 51፡1-2**
- “የእግዚአብሔርን ቃል የተናገሯችሁን ዋኖቻችሁን አስቡ፥” **ዕብ. 13፡7**

እመቤታችን ቅድመ ጸኒስ

- **በአምላክ ህሊና ታስባ ትኖር ነበር**
- እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ዓለም ከመፈጠሩ በፊት በአምላክ ኅሊና ታስባ ትኖር ነበር ። ይህንንም ሊቁ ቅዱስ ያሬድ « ዘእንበለ ይትፈጠር ሰማይ ወምድር. ወዘእንበለ ትሣረር ምድረ ገነƒ. ሀለወት ስብሕት ቅድስት ወቡርክት ይእቲ ማርያም. እንተ ተሰምየት ሰንበተ ክርስቲያን ፣ ጽዮን ፣ ቅድስት፣ እሞሙ ለሰማዕት ወእኅቶሙ ለመላእክት
- ዳግመኛም « በቤተ ልሔም ተወሊደ መድኅን ክብረ ቅዱሳን . ፍስሐ ለኵሉ ዓለም. ወሠርዐ ሰንበተ ለሰብእ ዕረፍተ. ወይቤለ እግዚአብሔር ለማርያም ፡- አዝማንየ አዝማንከ አምጣንየ አምጣንኪ. ማርያም ሐቀፍኪዮ ወአነ ዮም ወለድክዎ ። ለዓለሙ ኹሉ ደስታ የሚሆን የቅዱሳን ክብር መድኃኔዓለም በቤተልሔም ተወልዶ ፡- ለሰው ልጅ ዕረፍት ሰንበትን ሠራ

እግዚአብሔር እመቤታችን

- ዘመኖቹ ዘመኖችሽ. መጠኖቹ መጠኖችሽ ናቸው ፤ እኔ ዛሬ ወለድኩት፡- ማርያም ሆይ አንቺ ታቀፍሺው ።።
- ቅዱስ ያሬድ እንደገለጠው እግዚአብሔር እመቤታችንን « ዘመኖቹ ዘመኖችሽ ናቸው ፤» ማለቱ ዓለም ከመፈጠሩ ዘመን ከመቆጠሩ በፊት በእርሱ ኅሊና መኖረን የሚያስረዳ ነው።።
- መጠኖቹ መጠኖችሽ ናቸው ፤» ማለቱ ደግሞ እርሱ ቅድመ ዓለም አካላዊ ቃል ወልድን ያለ እናት ወልዶ አባት እንደሆነው እርሷም ድኅረ ዓለም አካላዊ ቃል ወልድን ያለ አባት ወልዳ እናት እንደሆነችው የሚያመለክት ነው ።።
- ምሥጢሩም (አባትና እናት) ለወለዱት ልጅ እኩል እንደሆኑ ሁሉ ወልድን በመውለድ በወላጅነት መሰልሸኝ ተስተካከልሺኝ ፤ » ሲለት ነው

ድንግል ማርያም በዓለመ መላእክት

- የመላእክት እኅት

  ሚካኤል መላክ በክነፍጾራ መንጦላእተደመና ሰወራ ታላቅ ምልክት በሰማይ ታየ ፤ » ራእ ፲፪ ፥ ፩ - ፪

- ቄድስዋ መላእክት ለማርያም በውስተ ውሳጤ መንጦላእት

- ሁር አብስራ ለወለተ ሃና

ከሱራፌል፣ ከኪሩቤል፣ ከመላእክት ትበልጣለች።።

- እርሷ ተሸክማዋለች፣ ጡቷን አጥብታዋለች፣ አዝላዋለች . . .
- እናቱ ተብላለች
- ልሳነ ኪሩቤል ኢይክል አብጽሖ ውዳሴኪ ወአፈ ሱራፌል ኢይፌጽም ነጊረ እበየኪ

  የኪሩቤል አፍ ምስጋናሽን መፈፀም አይቻለውም በሱራፌል አንደበትም ልዕልናሽ ድንቅነትሽ ተነግሮ አያልቅም (ሰዓታት ዘሌሊት)
-

እመቤታችን በአዳም ባሕርይ ውስጥ

❖ « ማርያምሰ ተነቱ እምትካት ውስተ ከርሱ ለአዳም. ከመ ባሕርይ ጸአዳ፤እመቤታችን ማርያም ከጥንት ጀምሮ በአዳም ባሕርይ ውስጥ እንደ ነጭ ዕንቁ ታበራለች እመቤታችን በአዳም ባሕርይ ውስጥ እንደ ነጭ ዕንቁ ማብራቷ ከጥንተ አብሶ ነፃ ሆና መፈጠሯን የሚያመለክት ነው።

❖**እንቲ ውእቱ ተሰፋሁ ለአዳም አመ ይሰደድ እም ገነት** ከገነት በተሰደደ ጊዜ የአዳም ተስፋው እንቺ ነሽ ብሏታል አምስት ቀን ተኩልም የተባለው አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ነው።።

❖ይህ እንደተፈፀመም ቅ/ጳ ነገር ግን የዘመኑ ፍፃሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ከሕግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ።(ገላ 4፥4

- የዘመን ፍፃሜ ብሎ አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመንን
- ሴት ብሎ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን
- ልጅ ብሎ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስን አነሳ።

<u>የኖህ መርከብ</u> ዘፍ 7፥2-23

- ኖህ በእግዚአብሔር ትዕዛዝ ሊመጣ ካለው ጥፋት ለመዳን መርከብን አዘጋጀ እርሱ ሚስቱ እና ሴም ካም ያፌት የተባሉ ልጆቹ ከነ ሚስቶቻቸው ከየወገኑም የተመረጡ እንስሳት ሁሉ ወደ መርከቧ ገቡ በዚህም ከጥፋት ውኃ ዳኑ::ዘፍ 7፥2-23::
- “ኖህ ገና ስለማይታየው ነገር ተረድቶ እግዚአብሔርን እየፈራ ቤተሰቦቹን ለማዳን መርከብን በእምነት አዘጋጀ በዚህም ዓለምን ኮነነ በእምነትም የሚገኘውን ጽድቅ ወራሽ ሆነ::ዕብ 11፥7::እንዲል ኖህ በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ ያገኘ በትውልዱ ጻድቅ ፍፁምም ሰው ነበር አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር በማድረጉ ፈጣሪው የሚድንበትን መንገድ አሳየው።

የአብርሃም ድንኳን

- በቀትርም ጊዜ እርሱ በድንኳን ደጃፍ ተቀምጦ ሳለ እግዚአብሔር በመምሬ አድባር ዛፍ ተገለጠለት ዓይኑንም አነሣና እነሆ ሦስት ሰዎች በፊቱ ቁመው አየ ባያቸውም ጊዜ ሊቀበላቸው ከድንካኑ ደጃፍ ተነስቶ ሮጠ ወደ ምድርም ሰገደ እንዲህም አለ አቤቱ በፊትህ ሞገስን አግኝቼ እንደሆነ ባርያህን አትለፈኝ::ዘፍ 18÷1-5::
- ቅዱስ አብርሃም በዚህ ምድር ቤት አልነበረውም የሚኖረው በድንኳን ነበርና በድንኳን ደጃፍ ተቀምጦ ሳለ ሥላሴ በሰው አምሳል ተገለጡለት እነሆ ለእርሱ በሃይማኖት ሥላሴ መሆናቸው ተገልጦለት ስለነበረ በግንባሩ ተደፍቶ የአምልኮት ስግደት ሰገደላቸው በአክብሮትም ተቀበላቸው ወደ ድንካንም እንዲገቡ በባለሟልነቱ ተማፀናቸው አስተናገዳቸውም ሥላሴ ወደ አብርሃም ድንኳን ገብተው ተስተናግደውለታል::

የሲና ሐመልማል ዕፀ ጳጦስ ዘፀ3፥1-6

❖ሙሴም የምድያምን ካህን በጎች ይጠብቅ ነበር ወደ ምድረ በዳም ዳርቻ በጎቹን ነዳ ወደ እግዚአብሔርም ተራራ ወደ ኮሬብ መጣ የእግዚአብሔርም መልአክ በእሳት ነበልባል በእሾህ ቁጥቋጦ መካከል ታየው እነሆም ቁጥቋጦው ስለምን አልተቃጠለም ይህን ታላቅ ራዕይ ልይ አለ እግዚአብሔር እርሱ ይመለከት ዘንድ እንደ መጣ ባየ ጊዜ እግዚአብሔር ከቁጥቋጦው ውስጥ እርሱን ጠርቶ ሙሴ ሙሴ ሆይ አለ እርሱም እነሆኝ አለ ወደዚህ አትቅረብ አንተ የቆምክባት ስፋራ የተቀደሰች መሬት ናትና ጫማህን ከእግርህ አውጣ አለው ደግሞም እኔ የአባትህ አምላክ የአብርሃም አምላክ የይስሐቅም አምላክ የያዕቆብም አምላክ ነኝ አለው ሙሴም እግዚአብሔርን ያይ ዘንድ ፈርቷልና ፊቱን ሸፈነ::ዘፀ 3፥1-6

❖አንቲ ውእቱ ዕፅ ዘርእየ ሙሴ በነደ እሳት ወኢትውኢ ዘውእቱ ወልደ እግዚአብሔር መጽአ ወነደረ ውስተ ከርስኪ ወእሳተ መለኮቱ ኢያዋየ ሥጋኪ (ቅ/ኤፍሬም)

የድንግልናዋ ምሳሌዎች

ገራህተ ሠሉስ ዘፍ 1፣11

ኦፈ ብርጋና አክ ዘሐ.

ተረክቦተ አዳም ዘፍ 1፣26

ህቱም ገቦ ዘፍ 2፣18

ወበከመ ብእሲት ተረክበት እምብእሲ 1ቆ

ህቱም እጸ ሣቤቅ ዘፍ 22፣13

ህቱም ኮኩህ ዘጸ17፣1-8

ህቱም ግብ ዘዳንኤል ዳን 13፣

ምንተ እብል ወምንተ እነብብ እስመ ናሁ ፣፣ሃይ 66፣20

በሰሚአ እዝን ዘእንበለ ዘርዐ ብእሲ ሃይ ቁር.71፣3



እመቤታችን

- በገነት ላለችው ዳግም ናት አንጻር ናት
- ከገነት ለወጣችው ቤዛ ናት
- ክርስቶስም በገነት ለነበረው ዳግም ነው
- ከገነት ለወጣው ግን ዳግማዊ ቤዛ ነው
- ለነፍሳት ካሣ ፣ለተነሳሕያን ደግሞ በቤዛም በካሣም በአርአያነትም ነውና ሦስቱ አይለዩትም።
- ግብር እምግብር ዕርገት እንጂ ሞት በማይስማማው ሔዋንነት የተገኘች ሕይወት ናትና።

በትንቢተ ነቢያት

- ሰው እናታችን ጽዮን ይላል
- በውስጧም ሰው ተወለደ እርሱ ራሱም ልዑል መሰረታት:: መዝ 86፥5
- እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምም ፀወነ ኃጥአን ወፃድቃን ፀወነ ሥጋ ወነፍስ ናት ለጠላት ዲያብሎስ አሳልፋ የማትሰጥ የምዕመናን ወዳጅ አማላጅ በመሆኗ “ጽዮን” መባል ይገባታል:: ነቢዩ ቅ.ዳዊት እናታችን መባል እንዲገባትም ተናግራል በእውነት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በዮሐንስ ወንጌላዊ አማካኝነት የተሰጠችን በመሆና ሁል ጊዜ እናታችን እንላታለን::ዮሐ 19፥26::

በወርቅ ልብስ ተጎናፀፋና ተሸፋፍና ንፍሥቲቱ በቀኝህ ትቆማለች ልጄ ሆይ እዩ ጆሮሽንም አዘንብይ ወገንሽን የአባትሽን ቤት እርሺ

ንጉሥ ውበትሽን ወዷልና እርሱ ጌታሽ ነውና <u>መዝ 44፥9</u>

- ልበ አምላክ የተባለ ዳዊት በትንቢቱ “ንግሥት” ያላት ቅድስት ድንግል ማርያምን ነው ነቢዩ ዳዊት ከዘጠኝ መቶ ዘመን በኋላ ቅድስት ድንግል ማርያም ከእርሱ ወገን ከእርሱ ዘር እንደምትወለድ በእግዚአብሔር መንፈስ ተረድቶ “ልጄ ሆይ” ብሎም ጠርቷታል::
- “ንጉሥ” ያለው:- የባሕርይ አምላክ ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው::
- “ውበትሽን”ያለው:- ደግሞ ንጽሕናዋን፣ቅድስናዋን ፣ድንግልናዋን ነው::

የቀጠለ.....



- መኑ ይእቲ ዛቲ መሐ 6፣10
- መሥዋዕተ ወቁር..መዝ 39፣6
- ወሶበ አኮ..ኢሳ 1፣9
- አልብኪ፣መሐ 4፣8ወይብልዋ ቅድስተ ..ዕብ 9፣4
- ንጽሕተ ንጹሐን ከዊና..
- ወትቀውም ንግስት ..መዝ 44፣9
- ቀደሰ ማኅሮ ልዑል መዝ 46፣5
- መጽሐፍ ጽሕፍት ራእ 5፣1
- ወርኢኩ ባህረ እንተ ትመስል ከመ ማህው ወድምርት ይእቲ...ራእ 15፣2
- ብእሲት እንተ ትለብስ ፀሐየ...ራእ 12፣1
- ተፈስሒ ፍስሕት ኦ ምልእተ ጸጋ.. ሉቃ 1፣29

- "ቅድስት ይእቲ ቅድሳቲከ በመቅደስ ቅድስተ ቅዱሳን" ሕዋሳቶቿ ንጹሐን ከሚሆኑ ከእመቤታችን ተወልደህ የምትመሰገናት ምስጋና ክብርት ናት።።
  አረ/መን.....ሰብህዎ ለእግዚአብሔር ስብሐተ ሐዲሰ
- ጎቡአትየ ዘምስሌኪ ኢከሰትኩ ለሰብእ ቅ .ያ
- ህሊና አዳም ዘአልቦ ተውሳክ ህጸት ምጸት ያላገኛት
- መርስ ወዛህን ያላት

የቀጠለ....

- ወውእቱሰ ንጹሕ እምሰለስቱ ግብራት... ሱንት .ሃይ 110፣29
- እንተ ብኪ ተበትከ ማእሰረ ሔዋን ማሕመሚ ሃይ 68፣36
- ተፈስሒ አ ማርያም ምድር ንጽሕት ዘበጽሐኪ እግ..ሃይ 68፣37
- ድንግል ንጽሕት ዘእንበለ ውላጤ እንድህረ ወለደቶ ድንግልናሃ ተረክበ ዘካ.ሃይ 108፣31
- ወሶበ ረከበ ሥጋሃ ክብርተ ወነፍሳ ቅድስተ ፈጠረ ሎቱ መቅደሰ ሕያው..ሃይ ዮሐ.አፈ፣66፣14

የቀጠለ.....


- ብፅዕት አነቲ ኦእግዝእትነ ማርያም ወላዲተ አምልክ እስመ ለብፅዐትኪሰ አልቦቱ ትርጓሜ አረ.መን ድር..24
- መንፈስ ቅዱስ የሐድር ልእሌኪ በንጽሕና ወኃይለ ልዑል ይጼልለኪ በቅድስና ሃይ 88 ፣3
- ይህን ዓለም ከማወቅ የተለየች ከመዓርገ ልቡና ካልደረሱ በቀር የማያውቋት
- እምጽቡር ጽሩየ ገብራ ሃይ 53፣22
- ኢያእመረ እስመ ዘተፈጥረት እምጽቡር ጽሩየ ትከውን መቅደሱ ለእግዚአብሔር ሃይ 48፣31
- አይ ልቡና ወአይ ነቢብ ወአይ ሰሚእ ዘይክል ዓእምሮ ዝንቱምስጢር....

እመቤታችን ጊዜ ጸነስ

- በአማን ነጸረ እግዚአብሔር አብ... ቅ. ሕር.ቅዳ.

ንጽሐ ሥጋ

- ንጽሐ ነፍስ
- ንጽሐ ልቡና
- ከዊነእም ዘምስለ አመት
- ጽበተ ከርሥ ዘምስለ ርሒብ
- ፅንስ እንበለ ሩካቤ
- ሀሊብ ምስለ ድንግልና
- ኅቡዓትየ ዘምስሌኪ ኢከሰትኩ ለሰብእ ቅ.ያሬድ.
- ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያም ይህች ናት ።



ሰው ቅድመ ስህተት ድኅረ ስህተት

- ልጅነት
- ጣዕም
- ሕይወት
- ልሕቀት
- ዐቂበ ሕግ
- ዘመደ መልአክ
- ውሑድነት ዘኢየሐልቅ

ድኅረ ስህተት የበደል ዝርዝር

- ጥቅል ትንተ አብሶ
- ባርያዊ ውርሳዊ ኀጢአት
- ፍዳ መርገም
- ሞተ ሥጋ ሞተ ነፍስ
- ጽንተ ኀጢአት
- ቁራኝነት የባህርይ ጉስቁልና
- የሀልዮ የነቢብ የገቢር ኀጢአት
- ፍትወታት እኩያት ኀጣውእ ርኩሳት
- የግል ኀጢአት
- ምልአተ ኀጢአት
- ፍጹም ጽልእ ከእግዚአብሔር መለየት

ትምህረተ ገብርኤል

- እግዚአብሔር ሰው ለመሆን በወደደ ጊዜ በምልአት ያለ እርሱ የሌለበት ሳይኖር በመልአኩ አብሣሪነት እናቱን ያበሥር የነበረው ራሱ ቢሆንም መገለጡና መታየቱ መናገሩና ማብሠሩ ግን የቅዱስ ገብርኤል እንደሆነ ቅዱሳት መጻሕፍት ያስረዱናል።
- ቅዱስ ያሬድ **ገብርኤል መልአክ መጽአ ወዜነዋ ለማርያም ጥዩቀ ሰናየ ዜና ከመ ይመጽእ አምላክ ለእሌሃ** አምላክ በላይዋ ላይ ይመጣ ዘንድ መልአኩ ገብርኤል መጥቶ መልካም ዜናን ለድንግል ነገራት“። ድጓ ታህሳስ ፲፱ እንዳለ
- **“ገብርኤል ተፈነወ ጸዊሮ መልእክቶ ለድንግል ዜናዋ ለዋሕድ ምጽአቶ** ገብርኤል መልእክቱን ተሸክሞ ተላከ፤ ለድግልም የወልድን መምጣት ነገራት“።
- **ዘእምቅድመ ዓለም ሕላዌሁ ፈነዎ ለገብርኤል ይሰብክ ምጽአተ ዚአሁ** አኗኗሩ ከዓለም በፊት የሆነው እሱን ይሰብክ ዘንድ ገብርኤልን ላከው ።

- "እንዘ ትፈትል ወርቀ ወሜለተ አስተርአያ ገብርኤል ግብተ ወርቅና ፈትል ስትፈትል ድንገት ገብርኤል ታያት"። እንዳለ ቅዱስ ያሬድ
- ውስጣዊ ሥራ ማለት ሰው መጀመሪያ ሲፈጠር የነበረውን ንጽሐ ጠባይን ሳያሳድፉ ከበደል በፊት የነበረች ሔዋንን መስሎ መገኘት ጨለማ በነገሰበት ዓለም በመቅረዝ ላይ እንዳለች መብራት፣ በተራራ ላይ እንደተሰራች መንደር ሆና መታየት ማቴ ፭
- በጐሰቆለው በፍጡራን ባሕርይ መካከል እንደ እንቍ እያበራች ማንም ያልያዘው ንጽሕና ይዛ መገኘት፣ በዚህም ንጽሕናዋ ከበደል በፊት ለነበረው አካል ምስክር መሆን ነው።
- በአፍአዊና በውስጣዊ ግብር እግዚአብሔርን ስታገለግል በማደን እኔ የእግዚአብሔር አገልጋይ ነኝ አለች። እኔን አገልጋዩን እናቱ ሊያደርገኝ ከወደደ እነሆኝ አለሁ ብላ ራሷን ለትዕዛዝ አዘጋጀች። በእንቢታ የመጣ በደል በእሺታ እንዲወጣ ምክንያት ሆነች።
- ቀድሞ ከአዳም በኋላ ተገኝታ ዓለም የሚጠፋበት በደል እንዲመጣ ሴት ምክንያት ነበረች። አሁን ደግሞ ከዳግማዊ አዳም በሥጋ በፊት ተገኝታ ዓለም እንዲድን ምክንያት ትሆን ዘንድ እሺ አለች።
- በዚህም ወደዚህ ዓለም ሰውን ሊያድን የመጣው ክርስቶስን የባሕርይ አምላክ፣ ሕይወት፣ መድኃኒት ነው ብላችሁ እመኑ:: በእሱም ዳኑበት:: ተብለን ስንጠራ እሺ በማለት ወደ እርሱ እንቀርብ ዘንድ መሪ አስተማሪ ሆነች።

- አባ ይስሐቅ እንደገለጸው “ይቤ ርዕዩ ዘንተ ሶበ ጸውኦ እግዚአብሔር ለገብርኤል ሊቀ መላእክት በምስጢር ወይቤሎ ከመወልድየ ፍቁር ይፈቅድ ይረድ ውስተ ምድር ሐር ከመታስተዳሉ ሎቱ ማኅደረ እስመ ናሁ በጽሐ ጊዜሁ ለአዳም ከመያንስኦ ወይሚጦ ውስተ ፍስሐሁ ውእቱ ዘተንጉለ ውስተ ሲኦል ናሁ በጸሐ ጊዜሁ ከመይድኅን ረድ ወሁር ኀበ ማርያም ወለተ ዳዊት ድንግል ወቅድስት ወንጽሕት እስመ ሐተትክዎን ለኵሎን አንስት ወኢረከብኩ ውስቴቶን ዘከማሃ ብርሀተ ወንጽሕተ ወበእንተዝ ወልድየ ፍቁርየ ይነስእ እሜሃ ሥጋ ረድ ወአቅርብ ኀቤሃ ፍስሓ ከመኢትፍራሕ እምኔከ ወበለ ከመዝ ሰላም ለኪ ተፈስሒ ኦ ምልእተ ፀጋ እግዚአብሔር ምስሌኪ ወበውስተ ከርሥኪ የኀድር መድኅን
- የመላእክት አለቃ ገብርኤን እግዚአብሔር በምስጢር እንደ ጠራው ልጇ ወዳጇ ወደምድር ይወርድ ዘንድ ለሱ ማደርያን እንድታዘጋጅለት ሂድ በሲኦል ወድቆ የሚኖር አዳምን ሊያነሣው ወደ ደስታውም ሊመልሰው ያድነውም ዘንድ ጊዜው ደርሷልና ንዕድ ክብርት ድንግል ወደምትሆን ወደ ዳዊት ልጅ ሂድ ሴቶችን ሁሉ መረመርኳቸው እንደሷ ያለች ንጽሕት ብርሀት አላገኘሁም።
- ስለዚህ ልጇ ወዳጇ ከሷ ሥጋን ይነሳል ከሷ የተነሳ ሳትፈራ ወደሷ ወርደህ ደስታን አቅርብ እንዲህም በለት ፀጋን የተሞላሽ ሆይ ደስ ይበልሽ ሰላምታ ይገባሻል እግዚአብሔር ካንቺ ጋር ነው በማኅጸንሽም መድኅን ያድራል"። አባ ይስሐቅ ሳዊሮስ ዘእስሙናይን ገጽ ፪፷፱

- ለዚህችም ተዋሕዶ ቀዳማዊው በደኀራዊ ሥጋ፣ ደኀራዊው በቀዳማዊ ቃል እንዲዋሐድ ምክንያት እመቤታችን ናት። “
- ፈትለ ወርቅ ወፈትለ ሜላት አመ በአፀባዕትኪ ተባየፁ
  አምሳለ መለኮት ወትስብእት እንዘ ኢይሐጹ
  ማርያም ጸገይኪዮ እንበለ አብ በሰሚዐ ቃሉ ወድምፁ
  ለገብርኤል መልአክኪ ዘፍሱሕ ገጹ
- የወርቅ ፈትልና የሐር ፈትል በጣቶችሽ አንድ በሆኑ ጊዜ ሳይጐድል የመለኮትና የሥጋ ተዋሕዶ አምሳል ነው። የእውነተኛ ፀሐይ መውጫ ማርያም ሆይ ፊቱ ደስ የሚያሰኝ የመልእክተኛሽን የገብርኤልን ቃልና ድምፅ በመስማት ያለ አባት ጸነስሽው። ማኅሌተ ጽጌ
- ይህ በሥጋ ያለ አባት እንደ ተፀነሰ እመቤታችንም ያለ ወንድ ዘር እንደፀነሰችው የሚያስረዳ ቃል ነው። የመልአኩን ቃል በመስማቷ ብቻ አካላዊ ቃል በማሕፀኗ ተቀረፀ። ይህም ከአእምሮ በላይ ከሕሊና ምጡቅ ሆኖ የምናገኘው ነው። ምጡቅነቱም እንዲህ ነው።
- አካላዊ ቃል በዓለምነታቸው ዓለም ከሚኖሩ ሥላሴ አንዱ አካል ሲሆን
  ከእነሱ ሳይለይ በተለየ አካሉ ምልዐትነት ሳይጐድለው በምልዐት ሳለ፣
  ስፋሀነቱን ሳያጣ በስፍሃት ሳለ፣ ርቀቱን ሳያጠፋ በርቀት ሳለ፣ ምልዐትን በውስንነት፣
  ስፍሃትን በጥበት፣ ርቀትን በማዝፈት የገለጠበት መንገድ ነው። እመቤታችን የመልአኩን ቃል በመቀበል ይሁንልኝ ብላ ፈቃዷን ስትገልጽ የእሷን ፈቃድ መሠረት አድርጎ በፈቃዱ ተፀነሰ። መፀነሱም እንዲህ ነው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተዋሐደው ሥጋ ከቅድስት ድንግል ማርይም እንደሆነ ሊቃውንትን እንስማ።

- ድንግልም አምላክን በወለደች ጊዜ ለዓለም ሕይወትን አስገኘች። ዘአቡሊ ሃይ 41፡4ሃይ 30፡9
- ሕፃኑንና እናቱን ይዘህ ወደ ግብፅ ሸሽ እስክነግርህም ድረስ በዚያ ተቀመጥ። ማቴ 2፡13
- ሰማይና ምድር የማይወስነውን ድንግል በማሕጸኑዋ ወሰነችው። ሃይ 61፡31
- ምን እላለሁ ምን አናገራለሁ እነሆ ድንግል በድንግልና ጸንሳለች ወልዳለች እንዴት ግን አትበሉኝ። ሃይ 66፡20

- "ማርያም ኮነት ልማደ ለእለ ቀደሙ አበው
- ለቀደሙ አባቶቻችን ማርያም መምህርን ሆነች"። ቅዱስ ቂርሎስ ድ/ በዚህም ጊዜ ቃሏን ምክንያት አድርጎ አካላዊ ቃል በማሕፀኗ ተቀረጸ።
- ልብ እንበል አካላዊ ቃል ማለት ያ ቅድመ ዓለም ያለ ዓለምን በመሐል እጁ የያዘ ከሦስቱ አካላት አንዱ ወልድ ነው። እርሱም አስቀድመን እንደተናገርን በምልዓት፣ በስፋት፣ በርቀት፣ በኃይል ያለ ዓለመ ዓለም፣ ዘመነ ዘመን፣ መጋቤ ፍጡራን፣ አብ መንፈስ ቅዱስ የሚናገሩበት ቃላቸው ነው። አካላዊ መባሉም ያ የሚናገሩበት ቃል አካል ነው ማለት ነው።"በመጀመሪያ ቃል ነበረ" ዮሐ ፩፣፩ ተብሎ የተነገረለት
- መጀመሪያ የሌለው መጀመሪያ የሆነው ቃል ይሄ ነው ተብሎ በማይጠራ መጀመሪያነት ያለ ሲሆን አሁን ግን በዚህ ጊዜ፣ በዚህ ወር፣ በዚህ ቀን፣ በዚህ ሰዓት ተፀነሰ፣ ተወለደ ለመባል በቃ።
- በዚህም በቀዳማዊ ልደቱ እናት ሳታስፈልገው እንደ ተወለደ በደኃራዊ ልደቱ ደግሞ አባት ሳያስፈልገው ተፀነሰ።
- በቀዳማዊው ሳይፀነስ ተወለደ በደኃራዊው ግን ለመወለድ ተፀነሰ። በዚህ ፅንስ ሰውን ለማዳን የተደረገ ተዋሕዶን እንመለከታለን።

- አሁን እመቤታችን ያለችው በመጠነ እንስት ነው። የምትገኘውም በዓለም ውስጥ ነው። የፀነሰችው ግን ከመጠነ ፍጡራን ውጭ፤ ከዓለም በአፍአ የሚኖረውን ምሉዑን አካለ ቃል ነው።
- ይህ አካለ ቃል ዓለማት ሳይፈጠሩ፣ ዘመናት ሳይቆጠሩ፣ ይህ ነው ተብሎ በማይጠራ ዘመን ከአብ ሳያንስ፣ ወደ ኋላም ሳይሆን በባሕርየ መለኮት ያለ እናት ከአብ የተወለደ ነው። ለመወለዱም የዕለት ፅንስ መሆን አልቀደመውም። የመወለድ ድካምም አለገኘውም። "እም ኀበ አብ ወጽአ ቃል ዘእንበለ ድካም ቃል ከአብ ያለ ድካም ተወለደ" እንዳለ ቅዱስ ኤፍሬም።
- እንዲሁም ዓለም ከተፈጠረ ዘመን ከተቆጠረ በኋላ ሁለተኛ በዘመናት ውስጥ ካለች ድንግል ለመወለዱ ዘር አልቀደመውም። <<አግመረቶ ለቃል ኢቀደሞ ዘርዕ ለልደቱ ለመወለዱ ዘር ሳይቀድመው ቃልን ወሰነችው" እንዳለ ቅዱስ ኤፍሬም የዕለት ፅንስ ለመሆን ግን በቅቷል። ይህም የተፀነሰው አስቀድመን እንደተናገርን ከፀነሰችው በፊት የነበረው ነው። አሁን ግን የእርሷ ፅንስ ነው። ይህም በምሉዕነት ያለው ቃል ርቀቱን ሳይተው በእመቤታችን ማሕፀን እንግዳ ሆነ በሚታይ ሥጋም ተፀነሰ። በዚህም የሚታይ ሥጋ የማይታይ ቃልን ለመሆን በቃ።

- ለዚህም የከፈለ ያዋሐደ መንፈስ ቅዱስ ነው። ግብሩ ግን የአንድነት ነው።
ሊቁ አጠፎስም

- ዘተወልደ እም አብ ቃለ እግዚአብሔር ዘዕሩይ ምስለ አቡሁ ወመንፈሱ ቅዱስ ተትሕተ እንዘ ኢይቴሐት በመለኮቱ ፤ተትሕተ በፈቃዱ ወለብሰ አርአያ ገብር ዘአልቦቱ ሥጋ ፤ለብሰ ሥጋ በእንቲአከ ፤አ ብዕሲ ቃል ዘተሰብአ ዘኢይትገሥሥ በመለኮቱ ተገሠ በእንቲአከ ፤አ ብእሲ ዘአልቦቱ ጥንት በመለኮቱ ለብሰ ሥጋ ፍጹመ ፤ወዘኢያስተርኢ ለብሰ ሥጋ፤ ዘያስተርኢ ወዘኢይትዌለጥ ተገሠ በሥጋ ዘይትዌለጥ ወረሰዮ ዘኢይትዌለጥ"

- ከአብ የተወለደ ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ አንድ የሚሆን የእግዚአብሔር ቃል ሰው ሆነ በመለኮቱ መዋረድ ሳይኖርበት በፈቃዱ ተዋርዶ የተገዘ ባሕርይን ተዋሐደ ሰው ሆይ ሥጋ ያልነበረው እርሱ ለንተ ብሎ ሥጋን ተዋሐደ ሰው ሆይ በመለኮቱ አይዳሠሥ የነበረ ነፍስን ሥጋን ቃል ለንተ ብሎ ተደሠሠ በመለኮቱ ጥንት የሌለው እርሱ ጥንት ያለውን ፍጹም ሥጋ ተዋሐደ አይታይ የነበረ የሚታይ ሥጋን ተዋሐደ የማይለወጥ እረሱ በሚለወጥ ሥጋ ተዳሠሠ የማይለወጥም አደረገው ሃ/አበው ፶፣፪-፬

- ከዚህ እንደተረዳነው ምሉዑ አካላዊ ቃል ጠባብ ሥጋን፤ ረቂቅ ቃል ግዙፍ ሥጋን እንደተዋሐደ ነው።።በመዋሐዱም ግሩም ምስጢር ተገለጠ።።
- ይህም ግሩም ምስጢር ሰማያዊ ቃል ምድራዊ ሥጋን ለመዋሐድ ከላይ ወደታች የወረደ አይደለም።። በምልዓት ሳለ ተፀንሶ ምድራዊ ሥጋ ሰማያዊ ቃልን፤እንዲሆን አደረገው እንጅ።። ሰማያዊ ቃል ምድራዊ ሥጋን በመዋሐዱ ምድራዊ ሥጋም ሰማያዊ ቃልን ተዋሐደ እንጅ
- በመውጣት በመውረድ የተደረገ አይደለም።። "ኢፈለሰ እመካን ውስተ መካን ከመመለእክት እስመ እሙንቱ ይትሃጥኡ ሶበ ተፈነዉ ለመልእክት ውእቱሰ ነስአ ሥጋ እንዘ ምሉዕ ውእቱ በኩለሄ እንደ መለእክት ከቦታ ወደ ቦታ አልተንቀሳቀሰም እነሱ ለመልእክት በወጡ ጊዜ ይታጣሉና እሱ ግን በሁሉ ሞልቶ ሣለቅጽበት ከድንግል ሥጋን ነሣ"፡

መወያያ

ጊዜ ጸኒስ በምሥጢረ ሥላሴ ዘንድ ይህ በማን ይፈጸማል ለምን ?

- መክፈል ፣ማዋሐድ፣ማክበር
- መክፈል፣መወሐድ፣ክብር መሆን
- መክፈል፣መዋሐድ፣መክበር

ይህ ምሥጢርስ እንዴት ይታያል ?

- 1ኛ ከፍሎ ሳይዋሐድ ቢቆይ
- 2ኛ ተዋሕዶ ሳይከፈል ቢቆይ
- 3ኛ ከብሮ ሳይዋሐድ ቢቆይ
- 4ኛ ተዋሕዶ ሳይከብር ቢቆይ

ባንድ ጊዜ የሚከናወኑ..

- መክፈል ፣ማዋሐድ፣ማክበር የሶስቱም አፍአዊ ግብር
- መክፈል፣መወሐድ፣ክብር መሆን የወልድ ውሳጣዊ ግብር
- መክፈል፣መዋሐድ፣መክበር የሥጋ ገንዘብ
- ወልድስ በኩነት አከበረው እንላለን አብና መንፈስ ቅዱስ እንዴት አከበሩት ቢባል ማክበር የሶስቱም ናትና
- 1ኛ ከፍሎ ሳይዋሐድ ቢቆይ ጎደረ በብእሲ ያሰኛል
- 2ኛ ተዋሕዶ ሳይከፍል ቢቆይ እመቤታችን አምላክ ሆነች ያሰኛል
- 3ኛ ከብሮ ሳይዋሐድ ቢቆይ በማን ከበረ/በሌላ ከበረ/ ያሰኛል ወይም ክብር ከክብር ጋራ ተዋሐደ ያሰኛል
- 4ኛ ተዋሕዶ ሳይከብር ቢቆይ ዜገ፣ አካለ ቃል ክብር አልባ ይሆናል

❖ስለዚህ ሲከፍልም፣ ሲዋሐድም፣ ሲቀባም (ሲከብርም) አንድ ጊዜ ነው።"ሲቀባም ሲዋሐድም አንድ ጊዜ ነው"

ጽንሱን በተመለከተ

ከመ ሀፍ ዘይወጽ እምገጽ መ/ምሥ

ከመንህብ ዘእምቃል ንባብ ቅዳ.ሕር.

ከመ ቃል ዘይነብር በልብ ወይትአቆር በህሊና መዝ 44፣1..

በፋሳስ ዉስጥ እንዳለ ብርሃን

እመ ሔዋን ቀዳሚት ኮነት ድንግልተ ሃይ

ተስሥለ በትንተ አካል እንዘ ይትዋሐድ ቃል ምሥለ ሥጋ ሃይ
  ዮሐ.ዘእስክንድርያ

እመቤታችን ድህረ ጸኒስ ክብረ ድንግል

ለቤትከ ይደሉ ሰብሐት ክብረ ድንግል በሚል ርእስ ስለ እመቤታችን ስለ ቅድስት ድንግልማርያም ክብር ማለትም የተሰጣት ፀጋ ምን እንደሆነ የምንመለከትበት ነው። ለማሳየትምእመቤታችን የአምላክ እናት መሆኗን፣ ቅድስናዋን፣ ዘለዓለማዊ ድንግልናዋን የምንመለከትበትእና በሌላም ንዑስ ርእስ ወሊዳ ዋህደ ወተወሊዳአሀተ

የክብረ ድንግል መገለጫዎች የሆኑትን ማለትም ለአምላክ እናት ለእመቤታችን ስግደት እንደሚገባት፣ ምስጋና እንደሚገባት፣ እንዲሁም በስሟ ዝክር(መታሰቢያ) ማድረግ እንደሚገባ እና የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነቷ ቃል ኪዳኗ የሚገለጽበት ነው።

1.የአምላክ እናት መሆኗ

❖እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የአምላክ እናት መሆኗ ቅዱሳት መጻሕፍት የተመሰከረ ነው።ነቢየ እግዚአብሔር ቅዱስ ኢሳይያስ በትንቢቱ እንዲህ ብሎ ተናግሯል “ሕፃን ተወልዶልናልና ወንድ ልጅም ተሰጥቶልናልና አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል ስሙም ድንቅ መካር ኃያል አምላክ የዘለዓለም አባት የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል።ኢሳ 9÷6 ይህም ድንቅ መካር ኃያል አምላክ” ተብሎ የተነገረለት የባህርይ አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

❖ቅድስት ኤልሳቤጥም በመንፈስ ቅዱስ ተመልታ ድንግል ማርያም የአምላክ እናት መሆኗን ስትመሰክር **የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጣ ዘንድ እንዴት ይሆንልኛል** ብላለች።ሉቃ1÷43። ድንግል ማርያም በቅድምና ለነበረ አካላዊ ቃል ለእግዚአብሔር ወልድ እናቱ ናት።ዮሐ 1÷1-14 ከእርሷ የተወለደው ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ነው።የሐዋ.ሥራ 20÷80።

የእስክንድሪያው ሊቀ ጳጳስ አባታችን ቅዱስ ቄርሎስ “አማኑኤል የባሕርይ አምላክ እንደሆነ ንጽሕት ድንግልም አምላክን የወለደች እንደሆነች ሰው የሆነ የእግዚአብሔርንም ቃል እንደወለደች የሚያምን ሰው ቢኖር የተወገዘ ይሁን” በማለት ካወገዙ በኋላ ዳግመኛ በኋላ ዘመን ቅድስት ድንግል እርሱን በሥጋ ወለደችው ስለ እኛ ሰው የሆነ የእግዚአብሔርን ቃል ወለደችው ስለዚህም ቅድስት ድንግልን ወላዲተ አምላክ እንላታለን። ሃ.አበው ገጽ 277-305

2. ቅድስናዋ

❖እመቤታችን ከሁሉ ይልቅ ወላዲተ አምላክ በመሆኗ ከፍጥረታት ሁሉ የከበረች ናት ይህ ከእግዚአብሔር የተሰጣት ስለሆነችም ቅድስተ ቅዱሳን ከተለዩ የተለየች ትባላለች አምላካችን ልዑል እግዚአብሔር **እኔ ቅዱስ እንደሆንኩ እናንተም ቅዱሳን ሁኑ**።ዘሌ 19÷2 ብሎ እንደተናገረው በፈጣሪው አርአያና አምሳል ለተፈጠረው የሰው ልጅም በቅድስና የፈጣሪውን አርአያ መከተል ሃይማኖታዊ ግዴታው ነው።

❖ከዚህ ዓለም ቅዱሳን እና ቅዱሳት መካከል እንደ እመቤታችን ያለ በእርስዋ መጠን ፀጋን የተመላ በንጽሕናና በቅድስና የተዋበ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ የሆነና በልዑል ኃይልም የተጠበቀ ሰውነት ያለው የለም።ሉቃ 1÷28-36።

❖ይኸውም እመቤታችን ለአምላክ እናትነት የተመረጠች ድንግል በመሆኗ እና የአምላክ እናት እንደመሆኗ መጠን በሐልዮ በማሰብ፣በነቢብ በመናገር፣በገቢር በመከወን ንፅሐ ጠባይ ያላደፈባት ቅድስትና ቡርክት በመሆኗ ነው ስለዚህ

❖ራስዋ ወላዲተ አምላክ አስቀድማ በወንጌል ቃል እንደተናገረችው ትውልድ ሁሉ “ቅድስት ወብፅዕት” እያሉ ሲያመሰገኗት ይኖራሉ።ሉቃ 1÷48።

❖የሰው ልጅ ንጽሐ ጠባዩን በድቀተ ኃጢአት ምክንያት ከማደፉ በፊት የነበረው የተፈጥሮ ንጽሐ ሥጋ፣ንጽሐ ነፍስ፣ንጽሐ ልቦና ወይም የሐልዮ፣የነቢብ እና የገቢር ንጽሕና የቱን ያህል እንደ ነበር ማረጋገጥ የተቻለውም በእመቤታችን ንጽሕና ቅድስና ነው።ይኸውም እመቤታችን ከፈጣሪዋ በተሰጣት ምሉዕ ፀጋ መሠረት በውስጥ በአፍአ የነበራት ንጽሕናና ቅድስና ሁሉ ፍፁም ስለሆነ ነው።

❖አምላክን በድንግልና ፀንሳ በድንግልና የወለደች እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከአዳም ዘር የተላለፈ ኃጢአት (ጥንተ አብሶ) ያላገኛት መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የሌለባት ገና ከመወለዷ አስቀድሞ በአምላክ ሕሊና ታስባ ትኖር የነበረች በሰው ልማድና ጠባይ ከሚደርሰው ሥጋዊ አሳብና ፈቃድ የተጠበቀች፣ከተለዩት የተለየች፣ንጽሕተ ንፁሐን ቅድስተ ቅዱሳን ናት።መኃል4÷7።

❖ማህደረ መለኮት እንድትሆን አድርጓታል አምላክን ለመውለድ ያስመረጣትና ያበቃት ንጽሕናዋ ቅድስናዋ ነው።አባ ሕርያቆስም በቅዳሴው “እግዚአብሔር አብ በሰማይ ሆኖ ምሥራቁን እና ምዕራቡን ሰሜኑን እና ደቡቡን ዳርቻዎችን ሁሉ ተመለከተ እንደ አንቺ ያለ አልተገኘም ያንቺን ንጽሕና ወደደ ደም ግባትሽን ወደደ የሚወደውን ልጁን ወደ አንቺ ሰደደ።”ብሏል

❖ቅ.ዳዊትም በመዝ 131፥13 “እግዚአብሔር ፅዮንን መርጧታል ማደሪያው እንድትሆን አስጊጧታል።”ብሏል ይህም እመቤታችንን እግዚአብሔር ለእናትነት እንደመረጣት እና በንፅሐ ሥጋ፣በንፅሐ ነፍስ፣በንፅሐ ልቦና እንዳስጌጣት የሚያስረዳ ሀይለ ቃል ነው።

3 ድንግልናዋ

❖እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ከተለየች የተለዩ፣ከከበሩት የከበረች የሚያደርጋት ማኅተመ ድንግልናዋ ሳይለወጥ አምላክን በድንግልና ፀነሳ በድንግልና መውለዷ ነው።ማቴ 1÷18-20።እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ጌታን ከመፅነሷ በፊት፣በፀነሰች ጊዜ፣ከፀነሰች በኋላ፣ከመውለዷ በፊት፣በወለደች ጊዜ፣ከወለደች በኋላ ድንግል ናት እመቤታችን ከሌሎች ሴቶች ተለይታ እግዚአብሔር ከፈጠራት ጀምሮ በአሳብ በመናገርና በመሥራት ንጽሐ ጠባይ ያላደፈባት ንጽሕት ናት።

- “ድንግል” የሚለው ቃል በርግጥ ቅድስናዋን፣ንጽሕናዋን ብቻ ሳይሆን ልዩ መሆኗንም ያመለክታል በዓለም ከነበሩና ከሚኖሩ ሴቶች እንደ እመቤታችን ድንግልና ከእናትነት፣ እናትነትን ከድንግልና አስተባብራ የተገኘች ሴት የለችም።እመቤታችን ዘለዓለማዊ ድንግልና ያላት ናት መኃል 4÷15 ነቢዩ ሕዝቅኤል የተመለከተው ራዕይም እመቤታችን እናትና ድንግል መሆኗን ነው።ሕዝ 44÷3።
- በቅዱስ ወንጌልም ቅዱስ ሉቃስ እንዲህ ብሏል ቅዱስ ገብርኤል “ወደ እንዲት ድንግል ተላከ የዚያችም ድንግል ስም ማርያም ነው።”በማለት ስለ ድንግልናዋ ተናግሯል።ሉቃ 1÷26።ነቢዩ ኢሳይያስም “እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች።”ኢሳ 7÷14።በማለት ስምዋን እስከ ግብሯ ድንግል ብሏታል ።

- ዘፀነስኪዮ ለፍሕም በማኅፀነ ሥጋ ድኩም ድንግልናኪሰ እስከ ዘልፍ ኅቱም ማርያም ጥዕምቱ ስም በሰጊድ ሰላም፤ በደካማ ሥጋ ፍሕም የተባለ መለኮትን የፀነሸው ፣ድንግልናሽ ግን ለዘወትር ኅቱም ነው ስምሽ የሚጣፍጥ ማርያም ሆይ ስግደት ሰላምታ ላንቺ ይገባል።(አባ ጊዮርጊስ፣ ሰዓታት
- ከሊቃውንት መካከልም ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ ስለ እመቤታችን ዘለዓለማዊ ድንግልና እንዲህ ሲል ተናግሯል። “ሥጋ የሌለው እርሱ ሥጋዋን ተዋሕዶ እንደ ሰው ሁሉ ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን በጌትነቱ ሳለ በማኅፀኗ ተወሰነ። ከዚያ በኋላም የሚወለድበት ቀን ሲደርስ በማይመረመር ግብር በኅቱም ድንግልና ተወለደ ማኅተመ ድንግልናዋም አልተለወጠም ማኅተመ ድንግልናዋ ሳይለወጥ ተወለደ እንጂ።”ብሏል ሃ.አ ገፅ 212።

❖“አምላክን የወለደች ማርያም ለዘለዓለሙ ድንግል እንደሆነች መውለዷም የማይመረመር ድንቅ እንደሆነ ከወለደችም በኋላ በድንግልና ፀንታ እንደኖረች አስረዳ” ሲል የተናገረው ደግሞ አባታችን የአንጾኪያው ሊቅ ሊቀ ጳጳስ ቅዱስ ሳዊሮስ ነው ሃ.አ.ገፅ 375።

❖ቅዱስ ጀሮም ቅድስት ድንግል ማርያም መድኃኒታችንን ከወለደች በኋላ ድንግል አይደለችም ለሚሉ መናፍቃን መልስ በሰጠበት ድርሳኑ “ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተዘጋው በር እንዴት እንደገባ ይንገሩኝና ቅድስት ድንግል ማርያም በድንግልና ፀንሳ በድንግልና መውለዷን እነግራችኋለሁ” ብሏል።

❖ስለዚህ የእርሷ የድንግልና ምስጢር በሥጋዊ አዕምሮ ሊደርስባት የማይቻል ድንቅ ነው። ቅዱስ ኤፍሬምም ነቢዩ ሕዝቅኤል የተናገረውን ትንቢት ሲተረጉም እንዲህ ብሏል “ነቢዩ ሕዝቅኤል የመሰከረለት ድንቅ በሆነ ታላቅ ቁልፍ የተዘጋች ከኃያላኑ ጌታ በቀር ማንም ወደ እርሷ ገብቶ የወጣ የሌለ በምሥራቅ ያያት ደጅ የተባለች መድኃኒታችንን የወለደች ድንግል ናት እርሱን ከወለደች በኋላ እንደ ቀድሞው በድንግልና ኑራለችና መጥቶ ምሕረት ከሌለው ጠላት እጅ ያዳነን ጌታን የወለድሽ ሆይ የማኅፀንሽ ፍሬ የተባረከ ነው።አንቺ ፍፅምትና የተባረክሽ ነሽ የእውነት አምላክ በሆነ በክብር ባለቤት ዘንድ ባለሟልነትን አግኝተሻልና በምድር ላይ ከሚኖሩ ሁሉ ይልቅ ገናንነትና ክብር ላንቺ ይገባል።”በማለት በረቡዕ ውዳሴው አመስግኗታል።እኛም የድንግልናዋን ነገር በአንክሮ እያሰብን ለምኝልን ልንላት ያስፈልጋል።

4. <u>የክብረ ድንግል መገለጫዎች</u>

❖ክብር የሚለው ቃል ጌትነትንና ከፍተኛነትን የሚያሳይ ነው።ከሁሉ በላይ ክብር ያለው እግዚአብሔር ነው:: ክብሩም በሥራው ይታያል።

መዝ 18÷1፣ዘፀ16÷7፣ኢሳ6÷3።እግዚአብሔር ክቡር በመሆኑ የአሸናፊ የእግዚአብሔር እናት ቅድስት ድንግል ማርያም አንዳች ያልጎደለባት ምልዕተ ጸጋ ስለሆነች እግዚአብሔርም ከእርሷ ጋር ስለሆነ ክብርት ናት።እንኳን መልዕልተ ፍጡራን የሆነች እርሷ የእግዚአብሔር ፍጥረት ሁሉ ክቡር ነውና።

ሉቃ 2÷9፣1ቆሮ 11÷7÷1ቆሮ15÷41።

❖አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ክብሩን በተአምራቱ በደብረ ታቦር በትንሣኤውና በዕርገቱ ገልጧል።ዮሐ 2÷11፣ማቴ 17÷1፣1ጴጥ 1÷20 በኋላም በዳግም ምጽአቱ ይገለጣል።ማር 8÷38።የእናቱ የቅድስት ድንግል ማርያም ክብር ደግሞ የተገለጠው አምላክን በድንግልና ፀንሳ በድንግልና በመውለዷ ነው።ይህ ክብር ልዩ ነው።ምክንያቱም ከእርሷ በቀር የአምላክ እናት የሆነ የለምና ወደ ፊትም አይኖርም።

- እመቤታችንን አስቀድሞ ያከበራት ልዑል እግዚአብሔር ነው።ነቢያትም እግዚአብሔር በገለጠላቸው መንገድ በትንቢት መነፅር እያዩዋት ክብሯን ተናግረውላታል።የምሥራቹን ይነግራት ዘንድ ወደ እርሷ የተላከ ቅዱስ ገብርኤልም አብስሯታል።ቅድስት ኤልሳቤጥም መንፈስ ቅዱስ አነቃቅቷት የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጣ ዘንድ አይገባኝም ብላ አክብራታለች ዮሐንስም በራዕዩ “ፀሐይን ተጐናፅፋ ጨረቃ ከእግሮችዋ በታች ያላት በራስዋ ላይ አሥራ ሁለት ከዋክብት የሆነላት”። በማለት ክብሯን በሰማይ ከፍ ብሎ በማየቱ አክብሯታል።ራዕ 12÷1፣መዝ44÷9

1 ስግደት ለእመቤታችን

- የእመቤታችን ክብር (ማክበራችንን) ከምንገልጥበት መንገድ አንዱ ለእመቤታችን የሚገባ “የፀጋ ስግደት” ነው።አንዳንድ ሰዎች (ከሃይማኖት ውጭ የሆኑ) ለእመቤታችን የምናቀርበውን “የፀጋ ስግደት” ልክ ለአምልኮ (ለእግዚአብሔር ብቻ የሚሰገድ) ስግደት አድርገው ሲነቅፉት ይሰማሉ።ኦርቶዶክሳዊ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ግን ለእመቤታችን የምታቀርበው ስግደት የፀጋ (የአክብሮት) ስግደት እንጂ የአምልኮት ስግደት አይደለም ።
- ለእመቤታችን የፀጋ ስግደት መስገድ እንዲገባ ቅዱሳት መጻሕፍት ተባብረው አስረግጠው ተናግረዋል።ኢሳ 49÷22። “ወንዶች ልጆችሽንም በጫንቃቸው ላይ ይሸከሟቸዋል።ነገስታትም አሳዳጊ አባቶችሽ ይሆናሉ።እቴጌዎቻቸውም ሞግዚቶችሽም ይሆናሉ ግንባራቸውንም ወደ ምድር ዝቅ አድርገው ይሰግዱልሻል የእግርሽን ትቢያ ይልሳሉ”። ብሎ ነቢዩ ቅዱስ ኢሳይያስ አስቀድሞ ተናግሯል፣

❖በሌላም ሥፍራ ነቢዩ እንዲህ ብሏል “የእግሬን ሥፍራ እሰብራለሁ የአስጨናቂዎችም ልጆች አንገታቸውን ደፍተው ወደ አንቺ ይመጣሉ የናቁሽም ሁሉ ወደ እግርሽ ጫማ ይሰግዳሉ የእግዚአብሔር ከተማ የእሥራኤል ቅዱስ የሆንሽ ጽዮን ይሉሻል።ኢሳ 60÷13።

❖መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስም በሐዲስ ኪዳን ገና በእናቱ በቅድስት ኤልሳቤጥ ማኅፀን ሳለ በመንፈስ ቅዱስ የተመላ ስለነበር የእመቤታችንን ድምፅ ለኤልሳቤጥ በተሰማበት ቅጽበት የፀጋ ስግደት ለእመቤታችን ለቅድስት ድንግል ማርያም የአምልኮት ስግደት በማኅፀነ ድንግል ላለው ጌታ ለኢየሱስ ክርስቶስ ሰግዷል።ይህን ያስደረገ መንፈስ ቅዱስ ነው።ዛሬም የእግዚአብሔር መንፈስ ያልተለየው ሁሉ ለእመቤታችን ክብር ይንበረከካል ይሰገድለታልም።ሉቃ 1÷15፣ሉቃ1÷39-46።

2.ምስጋና ለእመቤታችን

- በቤተ ክርስቲያናችን በመዝሙራችንም ሆነ በቅዳሴያችን ከስመ ሥላሴ ቀጥለን የምንጠራው የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያምን ስም ነው።
- እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በብሉይ ኪዳን ክብሯ እና ልዕልናዋ በነቢያት ሲነገር የኖረ በሐዲስ ኪዳንም ከእመቤታችን ከድንግል ማርያም በቀር “ደስ ይበልሽ ፀጋ የመላብሽ ሆይ ጌታ ከአንቺ ጋር ነው አንቺ ከሴቶች መካከል ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ” ተብሎ የተመሰገነ ማንም አልነበረም

ሉቃ 1÷28።

❖እመቤታችን እራሷ “ከእንግዲህ ወዲህ ትውልድ ሁሉ ያመሰግኑኛል’’ ብላ ተናግራለች (ሉቃ 1÷48)። ይህም ማለት ትውልደ ሴም፣ትውልደ ካም፣ትውልደ ያፌት ንዕድ ነሽ ክብርት ነሽ እያሉ ያመሰግኑኛል ማለቷ ነው።ከዚህ የወጣ ትውልድ የለምና እንዲህ ብላ በተናገረችው መሠረትም በልጇ የመንን ኦርቶዶክሳዊያንም መመኪያ ዘውዳችን ጥንተ መድኃኒታችን የንፅህና መሠረታችን ድንግል ማርያም ናት ብለን እናመሰግናታለን።

❖አምላካችን እግዚአብሔር ለወዳጁ ለአብርሃም “ታላቅ ሕዝብ አደርግሃለሁ፣እባርክሃለሁ፣ ስምህንም አከብረዋለሁ።ለበረከትም ሁን የሚባርኩህንም እባርካለሁ፣የሚረግሙህንም እረግማለሁ የምድር ነገዶች ሁሉ በአንተ ይባረካሉ።ዘፍ 12÷1-3። ብሎታል ከዚህ የእግዚአብሔር ቃል የምንማረው የቅድስተ ቅዱሳን የድንግል ማርያም ስም ክቡር መሆኑንና ብናመሰግናት በረከትን እንደምናገኝ ብንነቅፋት መርገምን እንደምንቀበል ነው።

አባ ሕርያቆስ፦

- "አ ማርያም በእንተዝ ናፈቅረኪ ወናብየኪ እስመ ወለድኪ ለነ መብልዕ ጽድቅ ዘበአማን ወስቴ ሕይወት ዘበአማን" ትርጉም፦ ማርያም ሆይ ስለዚህ እንወድሻለን ከፍ ከፍም እናደርግሻለን እውነተኛ የሕይወት መብልንና እውነተኛ የሕይወት (መጠጥ) ክርስቶስን ወልደሽልናልና
- "አ ድንግል ምልዕተ ውዳሴ በመኑ ወበአምሳለ መኑ ናስተማስለኪ" ትርጉም፦ ምስጋናን የተመላሽ ሆይ በማን እና በምን ምሳሌ እንመስልሻለን?
- ንትነሣእ በፍርሃተ እግዚአብሔር ከመ ናዕብያ ወንወድሳ ለምመዕተ ውዳሴ እንዘ ንብል አ ምልዕተ ጸጋ አ ሙኃዘ ፍሥሃ ፈድፋደ ብኪ ግርማ ራረእይ ዘየዐቢ እምኪሩቤል እለ ብዙኃት አዕይንቲሆሙ ወሱራፌል እለ ሰደስቱ ክነፊሆሙ፤ ምስጋናን የተመላች ድንግልን እናመሰግናት ዘንድ እግዚአብሔርን በመፍራት እንነሳ፤አይናቸው ብዙ ከሆኑ ክንፎቻቸውም ስድስት ከሆኑ ከኪሩቤልና ከሱራፌል የሚበልጥ ግርማ ባንቺ ተፈጽ ሟልና እያልን እናመሰግናት።

3. <u>የእመቤታችን ቃል ኪዳን አማለጅነት እና መታሰቢያ (ዝክር)</u>

በዚህ ክፍለ ትምህርት ሦስት ዓበይት ርዕሶችን ይዘ እንመለከታለን እነርሱም

ሀ. የእመቤታችን ቃል ኪዳን

ለ. የእመቤታችን አማላጅነት

ሐ. በእመቤታችን ስም (ዝክር) መታሰቢያ ማድረግ

<u>ሀ.የእመቤታችን ቃል ኪዳን:-</u> “ቃል ኪዳን” ትርጓሜው ውል ስምምነት መሐላ የሚል ሲሆን በቃል ኪዳን ውስጥ ቃል ኪዳኑን ሰጪ፣ቃል ኪዳኑን ተቀባይ፣በቃል ኪዳኑ ተጠቃሚ የሚሆኑ እንዳሉ ያስረዳል ።ይህን ሀሳብ ግልፅ ለማድረግ ቃል ኪዳን ሰጪ አምላካችን ልዑል እግዚአብሔር ሲሆን ቃል ኪዳኑን ተቀባይ እመቤታችን እና ሌሎችንም በተጋድሎ እግዚአብሔርን ደስ ያሰኙ ቅዱሳን ናቸው ።በቃል ኪዳን ተጠቃሚ የሚሆኑት ደግሞ በቅዱሳን በእመቤታችን ቃል ኪዳን ይሆንልኛል ብለው ያመኑ ሁሉ ናቸው ። ከመረጥኳቸው ጋር ቃል ኪዳን አደረግሁ።መዝ 88÷3 እንዲል።

❖እግዚአብሔር አምላካችን መዓቱን በምሕረቱ ቁጣውን በትዕግስቱ በመግታት የሰውን ሕይወት ለዘለዓለሙ ለመጠበቅ ሲል በመጀመሪያ በስሕተቱ ከተፀፀተው ከአዳም ቀጥሎ በዓድቅነቱ ከጥፋት ውኃ ለመዳን ከቻለው ከኖህ ከዚያም በእምነቱ በምግባሩ ቀናነት የእግዚአብሔር ወዳጅ ተብሎ ከተሰየመው ከአብርሃም ጋር ለመላው የሰው ዘር ሁሉ የሚሆን የምሕረትና የበረከት ቃል ኪዳን ገብቷል።ዘፍ 9፥11-17 ፣ ዘፍ12፥1።

❖ከዘመነ ብሉይና ከዘመነ ሐዲስ ቅዱሳን መካከል ከፍተኛው ፀጋና ክብር የተሰጠውም የአምላክ እናት ለሆነችውና በዚህም “ከፍጡራን በላይ ከፈጣሪ በታች” እየተባለች ለምትጠራው እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ስለሆነ ሌሎች የብሉይና የሐዲስ ኪዳን ቅዱሳንና ቅዱሳት ከተሰጠው ቃል ኪዳን ይልቅ ለእመቤታችን የተሰጠው ከሁሉም በላይ የበለጠ /የላቀ/ነው።

❖“ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሃለሁ”የሚለው የምሕረት ቃል ኪዳን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ለአዳም የቃል ኪዳን ልጅ መሆኗን የሚያረጋግጥ ሲሆን መስቀሉን በሞቱ አዳምን ለማዳን ከአዳም የልጅ ልጅ የተወለደው መሢህ ኢየሱስ ክርስቶስ በልደቱ በሞቱ ዓመተ ኩነኔን በዓመተ ምሕረት ለመተካት አስቀድሞ የገባውን ቃል ኪዳን ፈፅሞአል።

❖በመሆኑም በመልዕልተ መስቀል ስለ እኛ ድኅነት ተሰቅሎ ሳለ በመስቀሉ ስር የልጇን መከራ እየተመለከተች ልብን በሚነካ ሐዘን ስለ ልጇ ታለቅስ የነበረች እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም እና ይወደው የነበረ ደቀመዝሙሩ ቅዱስ ዮሐንስ ነበሩ ጌታችንም የሚወዳት እናቱን ለሚወደው ደቀ መዝሙሩ እነሆ ልጅሽ አለ ይህ የተነገረው የአደራ ቃል ደግሞ እመቤታችን በእርግጥ ለሐዲስ ኪዳን ምእመናን የተሰጠች የቃል ኪዳን እና የድኅነት ምክንያት የሆነች እናት መሆኗን ነው ።

❖ በዚህ መሠረትም እመቤታችን ፀጋን ሁሉ የተመላች የቃል ኪዳን እናት እንደመሆንዋ መጠን በማያሳብል የእናት አማላጅነቷ ጸጋን የምታሰጥ ልዕልተ ምሕረት ስለሆነች በስሟ ተማኅፅኖ ማድረግ እንደሚገባ አበው ያስተምሩናል።

ለ.<u>የእመቤታችን አማለጅነት፡-</u> የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት እንደ እንግዳ ደራሽ እንደ ውሃ ፈሳሽ በልብ ወለድ የሚነገር ሳይሆን መፅሐፍ ቅዱሳዊ ነው።መዝ 44÷9። “ንግስቲቱ ወርቅ ዘቦ ግምጃ ደርባ እና ተጎናጽፋ በቀኝህ ትቆማለች በማለት ተናገረ ትቆማለች ማለቱ ለአማላጅነት ነው።ምዕመናን ምግባር ጎድሎባቸው በልጇ ፊት የሞት ሞት የሲኦል ፍርድ እንዳይፈረድባቸው ልጄ ማርልኝ የገባህልኝን ቃል ኪዳን አስብ እያለች በቀደመ ልመናዋ የምታሰማራቸው (የምታማልዳቸው) መሆኑን መናገሩ ነው።

❖የእመቤታችንም ሆነ የቅዱሳን ምልጃ የታዘዘውና የተፈቀደው (ያስፈለገው) እግዚአብሔር ከጎጥአን ይልቅ የፃድቃን ጸሎት የበለጠ ስለሚሰማ ነው።የእግዚአብሔር ዓይኖች ወደ ፃድቃን ጆሮዎቹም ወደ ጩኸታቸው ናቸው።መዝ 33÷15።ተብሎ ተፅፎአል አማላጅነት የእግዚአብሔር የቸርነት ስጦታ ነው::

- የእናት አማላጅነት አያሳፍርም። ምክንያቱም የሰራኝታዋ መበለት ልጅ በሞተባት ጊዜ ለእግዚአብሔር ሰው ለኤልያስ ነግራ (አማልዳ) ከሞት እንዲነሳ አደረገች።1ነገ 17፥17-24።ሌሎችም ብዙ እናቶች ለልጆቻቸው ብዙ ነገር አድርገዋል ርብቃ ለያዕቆብ በጥበብ የአባቱን በረከት አሰጥታዋለች።ዘፍ 25፥ ከነቢያት ወገን የሆነች ሴት ባሏ በዕዳ የተበደረውን ሳይከፍል ቢሞት ልጆቿ በባርነት እንዳይያዙባት ለነቢየ እግዚአብሔር ለኤልሳዕ ነግራ ጥቂቱን ዘይት አበርክቶላት ያንን ሽጣ ዕዳዋን ከፋላ ልጆቿን ከባርነት ነፃ አውጥታለች 2ነገ 4፥25።ስለዚህ ከእናትም የምትበልጥ እናት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ምንም ምሳሌ የማይገኝላት እመቤታችን ታማልደናለችና በህይወታችን በአማላጅነቷ ሁል ጊዜ ልንጠቀም ያስፈልጋል::

ሐ.በእመቤታችን ስም መታሰቢያ (ዝክር) ማድረግ፡-በኢትዮጲያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም የክብር መገለጫ ከሆኑት ነገሮች መካከል በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም ሥም ዝክር መዘከር ነው::

❖“ዝክር” ትርጓሜው መታሰቢያ ማለት ሲሆን ይህ ዘለዓለማዊ መታሰቢያ ለወዳጆቹ ለቅዱሳን ይልቁንም ለእናቱ ለቅድስት ድንግል ማርያም እንዲደረግ የፈቀደ አምላካችን ልዑል እግዚአብሔር ነው። “እግዚአብሔር ሰንበቴን ስለሚጠብቁ ደስ የሚያሰኘኝንም ነገር ስለሚመርጡ ቃል ኪዳኔንም ስለሚይዙ ጃንደረቦች እንዲህ ይላል::በቤቴና በቅጥር ውስጥ ከወንዶችና ከሴቶች ልጆች ይልቅ የሚበልጥ መታሰቢያና ስም እሰጣቸዋለሁ ኢሳ 56፥4እና5 እንዲል።

❖ጌታችንም በቅዱስ ወንጌል “ዳድቅን በዳድቅ ስም የተቀበለ የዳድቁን ዋጋ ያገኛል እውነት እላችኋለሁ በቀደ መዝሙሩ ስም ቀዝቃዛ ፅዋ ውሃ የሰጠ ዋጋው አይጠፋበትም” ማቴ 10÷41::ብሎ እንደተናገረ በዳድቃን በቅዱሳን ስም የተመፀወተ (የተሰጠ) የማይጠፋ ዘለዓለማዊ ዋጋ የሚያሰጥ ከሆነ የዳድቃን የቅዱሳንን አምላክ የወለደች የእመቤታችንን ስም ለሚጠራ የሚመፀውትማ የበለጠ ዋጋ ይሰጠዋል ማለት ዋጋው አይጠፋበትም።

❖ለእመቤታችን ለቅድስት ድንግል ማርያም በተአምረ ማርያም መቅድም እንደተጻፈ በሕግ የተወሰኑ 33 በዓላት አሏት::እነዚህን በዓላት ምክንያት አድርገን በስሟ የተራበ ልናበላ የተጠማ ልናጠጣ የታረዘ ልናለብስ የተጨነቀ ልናረጋጋ ለቤተ ክርስቲያን ዕጣን ጧፍ፣ዘቢብ የተለያዩ ንዋየ ቅድሳት ልንሰጥ በአጠቃላይ በጎ ሥራ ልንሰራ ያስፈልጋል:: ይህንን በጎ ሥራችንን ወደ ልጇ አቅርባ የኃጢአት ሥርየት ታሰጠናለች:በኋላም እረፍት መንግስተ ሰማያት ታኖረናለች።

- ጌታችን በቅዱስ ወንጌል እንዲህ ብላል “ምሳ ወይ እራት ባደረግህ ጊዜ እነርሱ ደግሞ በተራቸው ምናልባት እንዳይጠሩህ ብድራትህንም እንዳይመልሱልህ ወዳጆችህና ወንድምችህን ዘመዶችህንም ባለጠጎች ጎረቤቶችህንም አትጥራ ነገር ግን ግበዣ ባደረግህ ጊዜ ድሆችንና ጉንድሾችን አንካሶችንም ዕውሮችንም ጥራ የሚመልሱት ብድራት የላቸውምና ብፁዕ ትሆናለህ በፃድቃን ትንሣኤ ይመለስልህልና።”ሉቃ 14÷12-14።እንዲል።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

ወለወላዲቱ ድንግል

ወለመስቀሉ ክቡር